# የሰንደቃችን በኢትዮጵያችን ይዞታ

*መንግስቱ ሙሴ*

**11/2/16**

*ሳኦ፣ ሴኔጋል፣ ማሊ፣ ጋና፣ ሁለቱ ጊዩንያ፣ኮንጎ፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ካሜሮን፣ ቤኒን፣ እና ኢትዮጵያን ጨምሮ 12 ሀገራት ተመሳሳይ የሰንደቅ አላማ ቀለማት ሲኖራቸው። አምስት አገራት ደግሞ ከቅኝ ገዥወች ከወሰዷቸው ሁለት ወይንም አንድ ቀለም ጋር በመደረብ ሶስቱን ቀለማት ይጋራሉ። በጥቅሉ ወደ 17 የሚደርሱን ከ 1950 በኋላ ከቅኝ ግዛት ተላቀው ነጻነታቸውን የተቀዳጁ የአፍሪካ አገራት ተመሳሳይነት ያለው ቀለማት ሰንደቅ አላማ አላቸው ማለት ነው።*

*በተለየም የፓን አፍሪካ ጽንሰ ሀሳብ ፈጣሪወች የጋናው የመጀመሪያ መሪ ክዋሜ ንክሩማህ እና የኮንጎው ፓትሪስ ሉሙባ የአገሮቻቸውን ሰንደቅ አላማወች ምንም ሳይጨምሩ በማዟዟር የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ሲወስዱ። እነዚህ የፓን አፍሪካ መሪወች ኢትዮጵያን የነጻነታቸው ምልክት አድርገው ይኮሩባት እንደነበር ይነገራል። በመሰረቱ አፍሪካን ከቀጥታ ቅኝ ግዛት ወደ የእጅ አዙር ባርነት ሊወስዷት ያሰቡት ምእራባውያኑ እነዚህን ሁለት ታላላቅ እና ደግ እራኢይ ለአፍሪካ ሕዝቦች የነበራቸውን ሰወች ብዙ ቆይተው ህልማቸው ስር እንዲሰድ ባለመፈለግ በግዜ እንደቀሰፏቸው ታሪክ የመዘገበው ነው። ኢትዮጵያ ከእራሷ በነጻነት መኖር አልፋ ለአፍሪካውያኑ የነጻነት ተጋድሎ ጧፍ እንደነበረች ብዙ መጓዝ አያስፈልግም።*

*የኔልሰን ማንዴላን "Long Walk to Freedom" የህይወት ታሪክ ማንበብ የኢትዮጵያን ለአፍሪካ ነጻነት የነበራትን የተሳትፎ ቦታ ለመረዳት ይቻላል። ዛሬ በህይወት ያለው የዜምባቡዬ የነጻነት ታጋይ እና ግንባሮች መሪወች ሮበርት ሙጋቤ ZANU እና ጆሹዋ ኑኮሞን ZAPU ን እና የዜምባቡየን እጣ ፈንታ ወሳኝ የሆነውን ትግል ኢትዮጵያ ባላት እና በሌላት አቅም የተወጣችው ሀላፊነት እንደነበር ግልጽ ነው። የጎረቤታችን ኬንያ እና መሪዋ ጆሞ ኬንያታ የኢትዮጵያውን ንጉሠ ነገስት እንደ ፈጣሪ ይመለከቱ የነበር መሪ እንደነበሩ፤ ለዚያ ክብር ምክንያታቸው ነጉሠ ነገስቱ ለአፍሪካ አህጉር ነጻ መውጣት የነበራቸውን ታላቅ ተሳትፎ በመገንዘብ መሆኑን ታሪክ ያወሳል።*

*በተጨማሪም የዛሬውን አያርገው እና ኢትዮጵያ የራሷን ነጻነት ከማንም አገር በፊት እና በላይ ጠብቃ እዚህ ብትደርስም። የዚህችን አገር የነጻነት ተጋድሎ እና ኩራት ማየት የማይፈልጉት በተለይም ምእራባውያኑ መናኛ ሀይሎችን እና ግለሰቦችን እየፈጠሩ አዝምተውብን ብሎም አገር እንድትፈርስ ትልቅ መረባረብ በማድረግ ዛሬ ላይ ከቆምንበት አድርሰዋል። ዛሬ አንዳንድ ወገኖች የአገራቸውን ታላቅነት እና የታላቅነት ታሪካዊ ተጋድሎ ጀርመኖች፣ ጥሊያኖች፣ እና አሜሪካኖች በሰጧቸው የተረት ተረት የአማራ ቅኝ ገዥነት ቲወሪ ወንድም እህታቸውን፣ ብሎም የእራሳቸውን ማንነት ገላጭ የሆነውን ታላቋን ሰንደቅ ሲያራክሷት እያየን ነው። ያሳዝናል። ከማንም በላይ አያቶቻቸው የወደቁላትን አገር እና የተሸከሟትን ሰንደቅ የእኔ አይደለም የሚሉ መፈጠር እጅግ አሳዛኝ ምን ያክል የአእምሮ ድህነት እንደተፈጠረ እንገነዘባለን። ግን ይህን ዘርዘር አድርጌ ላስረዳ*

*በሰንደቅ አላማ የሚደርሱ ግፎች*

*ሰንደቅ አላማን ማዋረድ በእርግጥም በእኛ የጀመረ አይደለም። አሜሪካ የ 242 አመት እድሜ ያላት አገር ናት። ሕገ መንግስታቸው የተረቀቀው ሁሉንም የፖለቲካ አስተሳሰቦች በማካተት እና መሰረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ በልደት ያገኛቸውን ነጻነቶች ተንተርሶ እና ሳይጋፋ ነው። እናም የሰንደቅ አላማቸውም ትርጓሜም በህገመንግስታቸው የተካተተ እዲሆን ተደርጎ ነው። ግን ከዘመን ዘመን በቀኝ ጽንፈኖች ወይንም በግራ ጽንፈኞች ሰንደቃላማዋ ስትዋረድ፣እንደ ጨርቅ ስትወረወር እና ስትቃጠል ተስተውሏል።*

*ለምሳሌ ዛሬም ድረስ የደቡባዊ አሜሪካ (ኮንፌደሬሽን) አምላኪ እና ተጋዳይ የነበሩ የልጅ ልጆች ያነን ሰንደቅ አላማ ሲያውለበልቡ ይታያል። ይህ ደግሞ በተለይ እኔ በምኖርበት ክፍለ ግዛት ቴክሳስ በብዛት ከጎረቤቶቻችን ጀምሮ በየቀኑ የምናየው ነው። neo-Nazi, የሚባሉት ዛሬም የ ጀርመኑን Third rich (ሶስተኛው ኢምፓየር) ምልክት በሰውነታቸው ጭምር ሲስሉት እናያለን። በግራ በኩል የግራ ጽንፈኛ ዛሬ እንኳን የለም ግን በአለፈው ምእተ አመት የመጨረሻ አጋማሽ እና ከሲቪል የነጻነት ንቅናቄ ጋር በተያያዘ የኮሚኒስቶች ምልክት የሆነውን ቀይ ሰንደቃላማ ከማጭድ መዶሻ ጋር ይጠቀሙበት እንደነበር በየታሪክ ጽሁፎች እናያለን። ይህ በእነርሱ ብቻ አልነበረም ኢትዮጵያም ውስጥ የግራ ፍልስፍና በተስፋፋበት ወቅት ከኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ጋር የቀዩን ከማጭድ እና መዶሻ ምልክት ተጠቅመናል።*

ይህ መቸም በሁሉም አገር የሚከሰት መሆኑ ነው። ዛሬ ልዩ የሚሆነው በኢትዮጵያ ያልነበሩ የዘር ሰንደቅ አላማወች መፈጠራቸው ነው። አልፎም ተርፎ እራስን እና ማንነትን የመካድ ታሪካው ሸፍጠት ሲሰራ፣ የሁላችንም አያቶች፣ ቅድመ አያቶች የተሸከሙትን እና ኮከብ ሆኖ የመራቸውን ብሎም ብዙወቹ ለብሰውት የወደቁለትን የኩራት፣ የጀግንነት ታሪካዊ ሰንደቅ የማዋረዱ አባዜ ነው።

ሁሎችንም ማለት ይቻላል፤ ዛሬ ምልክታቸው የሆነውን የዘር ሰንደቅ ምንነት ቢጠየቁ ሀሰት ፈጠራ ካልተጨመረበት ታሪካዊ የሆነ እና ገማጅ ታሪክ እንደማይኖረው በእርግጥ መናገር ይቻላል። ይህ አንዱ የብሄራዊ ቀውሳችን አካል መሆኑን መቸውንም ልንረሳ አንችልም። ይህን ግድፈት ለማረም ደግሞ ቁጭ ብሎ የመማማርን በይበልጥም ተተኪ ትውልድን እና አሁን በሕወሐት የጸረ ኢትዮጵያ ዘመን የደረሰውን ሁሉ በሰፊ ልቦና ለማረም መነሳሳት ይፈልጋል።

ተብሎ ያለቀለቱ የሕወሐት በኢትዮጵያ የፖለቲካ የበላይነት ገጠመኝ ስህተቱም በእኛው በዜጎች የተፈጸመ እርምቱም የእኛን ይሁንታ የሚጠይቅ ነው። አንድ ሕዝብ አገር ለሽህ አመታት ያደለበውን ባህላዊ እና የሚያስተሳስሩ እሴቶች በአንድ እና ሁለት ትውልዶች አራግፎ እንዲጥል የተሞከረው የጠላቶቻችን ደባ ዘላቂ ነው ባንልም ያደረሰው ጉዳት ግን ቀላል እንዳልሆነ እንረዳዋለን። ለሁሉም ከብዙ ስራወቻችን የመጀመሪያው የተፈታተነንን እንደ አገር መቀጠል መስመር ማስያዝ ሲሆን። ይህን ደግሞ ከፖለቲካ ሾኬ ወጥተን በአንድ እና ለአንድ አላማ ተነሳስተን ስንገጥመው መሆኑ ሊረሳ የማይገባው ጥብቅ ጉዳይ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!!!

**መንግስቱ ሙሴ**

http://www.ethiopanorama.com